# ጥናት አንድ ዕዝራ 1፡1-11(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እንደማንኛቸውም ነገሥታት ብዙ ሊያስብባቸው ለማከናወን የሚችላቸው ብዙ ዓይነት አንገብጋቢ ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ቢታወቅም እግዚአብሄር በልቡ ውስጥ ያኖረውን የሕዝቡን ከምርኮ ተመልሶ በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሄር ቤት የመስራቱን ነገር ቅድሚያ እንደሰጠው እንመለከታለን። ይህ የአህዛብ ንጉሥ ራሱ ከሚፈልገው አጀንዳ ውጭ እግዚአብሄር የሚፈልገውን አጀንዳ እንዲፈጽም የተደረገበትን መንገድ ቁ1 ሲነግረን "እግዚአብሄር የቂሮስን መንፈስ አነሳስቶ…" በማለት ነው የሚገልጽልን።
2. ይህ ንጉሥ በአገሩ ሁሉና በግዛቱ የሚኖሩት ማናቸውም ሕዝቦች የአይሁድን ሕዝብ ወደ ኢየሩሳሌም የመመለስ ጉዳይ አስመልክቶ እንዲያውቅና መታዘዝ ያለበትም ሁሉ እንዲታዘዝ ውሳኔውን ያስተላለፈባቸው ሁለቱ መንገዶች፤ የመጀመሪያው በቃል ዓዋጅ ማስነገር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ውሳኔው በጽሑፍ እንዲሰፍር ማስደረግ ነው። ለዚህ ጥያቄ ብዙ መልሶች ሊቀርቡ ቢችሉም፤ እኔ የሚመስለኝ የመጀመሪያው ምክንያት የነገሩን ወሳኝነትና ጥንካሬ ለማሳየት፣ ሌላው ደግሞ እግዚአብሄር ራሱ በኋላ ተቃውሞ እንደሚመጣባቸው አስቀድሞ ስለሚያውቅ በጽሑፍ እንዲቆይ ማድረጉና፣ ሶስተኛው ደግሞ የፋሬስ ደንብ ሆኖ ማናቸውም የንጉስ ውሳኔ በጽሑፍም መስፈሩ ግዴታ እንደሆነም አንብቤአለሁ።
3. ይህ ሰው በአፉ ለመናገር ብቻ ሳይሆን ሕጋዊ በሆነ ሰነድ ላይ እንኳን ለማስፈር እስከማይቸገርበት ድረስ ከልቡ የተቀበላቸው ሁለት ነገሮች ቢኖሩ፤ አንዱ እግዚአብሄር የምድርን መንግሥታት ሁሉ እንደሰጠው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በይሁዳ ምድር በምትገኘው በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሄር መቅደስን እንዲሰራለት እንዳዘዘው የሚናገረው ነው። ቤተ መቅደሱን እንድሰራለት አዞኛል የሚለው የቂሮስ አነጋገር በሥጋው እዚያ ተገኝቶ መቅደሱን ሰርቷል ማለት እንዳልሆነ የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህንን ማለቱ ግን፤ ዓዋጁ እንዲወጣና ሕዝቡ ሄዶ መስራት እንዲችል መፍቀድ፣ ለሥራው የሚያስፈልገው ነገር እንዲመቻች ማድረግና፣ ተቃዋሚ እንዳይኖር ማዘዝና የመሳሰሉትን በማድረግ ለመቅደሱ ሥራ ሁኔታን ማመቻቸትን ነው።
4. ንጉስ ቂሮስ ከእግዚአብሄር ተቀበልኩ የሚለውን የመቅደሱን ሥራ እንዲሰሩ በመንግሥቱ ውስጥ እየኖሩ ያሉትን አይሁዶች በሁለት በመመደብ ሲያናግር እናያለን፤ የመጀመሪያው ምድቦች መቅደሱን ለመስራት ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ በልባቸው የሚፈልጉት ሲሆን፣ ሁለተኛዎቹ ምድቦች ደግሞ በቁ4 ላይ የምናያቸው በአካል መቅደሱን ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆኑትን ነው። ለመሄድ የተዘጋጁትን ሰዎች ሄደው ጉልበታቸውን እንዲሰጡና እግዚአብሄር ከእነርሱ ጋራ እንዲሆን ምርቃት፣ የማይሄዱትን ደግሞ በበጎ ፈቃዳቸው ከሚሰጡት ባሻገር ሥራውን በብር፣ በወርቅ፣ በእቃና፣ እንስሳን በመስጠት እንዲረዱ ትዕዛዝ አስተላልፏል።
5. መቼም የሁሉንም ምክንያት ማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን፤ ከምክንያቶቹ መሃል ይሆናሉ ብዬ የማስባቸው፤ አዲስ ኑሮን የመጀመር ፍርሃት፣ የባቢሎን የኑሮ ምቾት፣ በመንፈሳዊ ህይወት መደንዘዝ፣ የተስፋ ቃሉን በጭራሽ አለማስታወስና የመሳሰሉት ሊሆኑ እንደሚችሉ እገምታለሁ። ንጉሱ ቂሮስ ቤተ መቅደስ እንዲሰራ የተነሳሳበት ምክንያትና፤ የይሁዳና የብንያም ቤተሰብ አለቆች፣ ካህናቱና ሌዋውያኑም ሁሉ ቤተ መቅደሱን ለመስራት ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የተነሱባቸውን ምክንያት ስንመለከት፤ ሁለቱም እግዚአብሄር ለዚህ ሥራ መንፈሳቸውን ያነሳሳቸው ሰዎች መሆናቸው ያመሳስላቸዋል።
6. የይሁዳና የብንያም ቤተሰብ አለቆች፣ እንዲሁም የካህናቱና የሌዋውያኑ ለመሄድ መነሳት አንዱ ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ለመሄድ ያልፈለጉትና እዚያው ለመቅረት የወሰኑት ጎረቤቶቻቸው ደግሞ በንጉሱ በታዘዙት መሰረት አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሶችን ሁሉ መስጠታቸው የአዋጁን ተፈጻሚነት ያስረዳናል።
7. ይህ ሁኔታ ሊያስተምረን የሚችለው ነገር፤ እግዚአብሄር ሊሰራ ከወደደ ሊጠቀምበት የማይችለው ሰውም ሆነ ማናቸውም ነገር ሊኖር እንደማይችልና እኛ ደህንነትን ሊያመጣልን ይችላል ብለን ከምናስበው ነገር ውጭ እርሱ ባልታሰበና ሊሆን ይችላል በማይባል መንገድ ሊመጣ እንደሚችል ያስተምረናል እላለሁ።

# ጥናት ሁለት ዕዝራ 3፥1-13(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የዚህ ታሪክ ተዋናኞች ሆነው የማያቸው፡ እስራኤላውያን፣ ኢያሱና ካህናት ዘመዶቹ፣ ዘሩባቤልና የሥራ ባልደረቦቹ፣ በዙሪያቸው የነበሩት አህዛብ ይገኙበታል። በእኔ መረዳት ዕዝራ በዚህ ክፍል ውስጥ "ሕዝቡ እንደ አንድ ሰው ሆነው በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ።" በማለት ሲናገር፤ ምንም እንኳን 50,000 የሚያህሉ ሰዎች ቢኖሩም እነዚህ ሁሉ በአላማና በአስተሳሰባቸው አንድ ሆነው አንድን ነገር ብቻ ለመስራት ያላቸውን የአንድነት መንፈስ ለማመልከት ነው።
2. ጳውሎስ የፊሊጵሲዩስን ሰዎች እየጠየቃቸው ያለው ነገር እንደ አንድ ሰው ሆነው ለወንጌል እንዲጋደሉ ሲሆን፤ እነዚህ ሰዎች ደግሞ እንደ አንድ ሰው ሆነው ለእግዚአብሄር አምልኮ የሚሆነውን ለመስራት መነሳታቸው ጳውሎስ ያለውን ሃሳብ በተግባር የተረጎሙ ሰዎች ሆነው አያቸዋለሁ።
3. እነዚህ በዚህ ሥፍራ ሥራውን የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ በተለይም ካህኑ ኢያሱና ሌሎቹም ካህናቶች እንዲሁም ዘሩባቤልና የሥራ ባልደረቦቹ ሁሉ ሥራውን ጥንቃቄ በተሞላው መልኩ መጀመራቸውን የሚጠቁመን "በእግዚአብሄር ሰው በሙሴ ሕግ በተጻፈው መሰረት" የሚለው በቁ2 ላይ የምናገኘው ሃሳብ የራሳቸውን ሃሳብ ሳይሆን የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመታዘዝ እንደቆረጡ ያስረዳናል። በእኔ አመለካከት ለመሰዊያው ቅድሚያ መስጠታቸው ሊያስተምረን የሚችለው ነገር፤ በህይወታችን እንደፈረሱ የምናውቃቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ እንኳን ቢሰማን ቅድሚያ ሰጥተን ልንሰራውና ልናበጀው የሚገባን አንድ ነገር ቢኖር አምልኳችን እንደሆነ ነው።
4. ከምርኮ የተመለሰው ህዝብ እግዚአብሄርን ለማምለክና ለመታዘዝ በውስጣቸው የነበረው ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የሚመጣባቸውን ማንኛቸውንም ነገር ለመቀበል ዝግጁ መሆኖቸው ሳይሆን እንደማይቀር ነው የማምነው። ይህ በዚህ ሥፍራ የሰሩት መሰዊያ መሰዊያ አለን ለማለትና ለታይታ ብቻ የተሰራ እንዳልነበረ የምንረዳው፤ ቁ4-6ትን ስናነብ በእግዚአብሄር ቃል በታዘዘው መሰረት የተለያዩ ዓይነት መስዋዕቶችን በማቅረብ ወዲያው ሥራ ላይ ሲያውሉት ማየት እንችላለን።
5. የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ሥራው የተጀመረው ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር እንደነበረ ቁ8 በግልጽ ይነግረናል። በዚህ ቦታ የማያቸው የሥራ ክፍፍል ዓይነቶች፤ የህንጻ ሥራ ተቆጣጣሪዎች፣ መሪዎች ወይም አለቆች (እነ ዘሩባቤልና ኢያሱ)፣ ግንበኞች (ቁ10)፣ ዘማሪዎች (ቁ10)
6. ለቤተ መቅደሱ መጀመር ለወቅቱ የተመረጠው መዝሙር ቁ11 ላይ የምናነበው "ቸር ነውና ለእስራኤልም ምህረቱ ለዘለዓለም ነውና።" የሚለው ዝማሬ ነው። በዚህን ወቅት በዝማሬው የመሩት ካህናቱ ይሁኑ እንጂ ከቁ11 እንደምንረዳው ሕዝቡ ሁሉ በእልልታና በምስጋና በዝማሬው እንደተሳተፉ እናነባለን።
7. የመቅደሱ መሰረት ሲጣል ያስከተላቸው ሁለት ዓይነት ሥሜቶች፡ አንደኛው የደስታና የዝማሬ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የሃዘንና የለቅሶ ስሜቶች ነበሩ። በደስታ የፈነደቁት የቀድሞውን ቤተ መቅደስ ያላዩ ወጣቶች ሲሆኑ፣ ያዘኑትና ያለቀሱት ደግሞ በእድሜ የሸመገሉና የቀድሞውን ቤተ መቅደስ ክብር ያዩት ሰዎች ናቸው።
8. በተለይም ቁ7 ላይ እግዚአብሄር ራሱ "ይህንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ" ብሎ ከተናገረ ከህንጻው ትልቅነት ይልቅ ትልቁ እግዚአብሄር የሚገኝበት ቤት ከሆነ የቀደመውን እያስታወሱ ማልቀስ ተቀባይነት የሌለው ነገር ነው ብዬ አምናለሁ።
9. ሰዎቹ ሁሉ በአንድ ልብ ሆነው እንደ አንድ ሰው ሆነው ለአንድ ዓላማ መሰለፋቸው ከፈለጉት ግብ ለመድረስ በጣም ረድቷቸዋል ብዬ አምናለሁ፤ ምክንያቱም አንዱ የመቅደሱን ሥራ እንጀምረው፣ ሌላው ደግሞ ጠላቶቻችን መጥተው የተሰራውን መሰዊያ እንዳያፈርሱብን ቅጥሩን በመጀመሪያ እንስራ፣ ሌላው ደግሞ ሌላ ነገር ይዞ ቢነሳ የዚያን ሰው ሁሉ ሃሳብ ለማስተናገድና እንኳንስ በአንድ ቀን ቀርቶ ወርም የሚበቃቸው አይመስለኝም፤ ስለዚህ አንድ መሆናቸው ትልቅ በረከት ነው ብዬ አምናለሁ።

# ጥናት ሶስት ዕዝራ 4፡1-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ቤተ መቅደሱን እኛም ከእናንተ ጋራ አብረን እንስራ በማለት ጥያቄ ያቀረቡትን ሰዎች ጸሐፊው በዚህ ክፍል ውስጥ በቁ1 ላይ “የይሁዳና የብንያም ጠላቶች” በማለት ነው ሲጠራቸው የምናየው። እነዚህ ከአይሁድ ጋራ የእግዚአብሄርን ቤተ መቅደስ በመስራት ለመተባበር የሚጠይቁት ሰዎች ስለእግዚአብሄር ሲናገሩ “እኛም እንደ እናንተ አምላካችሁን የምንፈልግ ነን” በማለት እርሱ የአይሁዶቹ አምላክ እንጂ የእነርሱ አምላክ እንዳልሆነ ይህ ንግግራቸው በግልጽ ያስረዳናል።
2. የአይሁድ ጠላቶች ከእግዚአብሄር ህዝብ ጋራ ተቀላቅሎ ቤተ መቅደሱን አብረው ለመሥራት መጠየቃቸውን ስናይና በቁ3 ላይ ዘሩባቤል፣ ኢያሱና፣ የእስራኤል ቤተሰቦች አለቆች በአንድ ድምጽ እንቢ አይሆንም ማለታቸው እነዚህ ያህዌን ከሌሎች አማልክቶቻቸው ጋራ አጣምረው ማምለክ የሚፈልጉ ሰዎች በመገንባቱ ከተሳተፉ ቆይተው በአምልኮውም የመሳተፍ መብት ይኖራቸዋል ማለት ስለሆነ ከመጀመሪያው መቅጨታቸው ትልቅ ብልህነት ነው እላለሁ። 2ኛ ቆሮ 6፡15ትን ማንበብ ይረዳል።
3. ለንጉሱ የተጻፈው ደብዳቤ ላይ በተባባሪነት ሥማቸው ሰፍሮ የምናያቸው ግሩፖች፡ አገረ ገዢው ሬሁም፣ ጸሐፊው ሲምሳይ፣ በተለያዩ ከተሞች ላይ ገዢዎችና ዳኞች የሆኑ ሰዎች፣ በሰማርያ ከተማና በኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ከሰፈሩት ሕዝቦች። በዚህ ሥፍራ የተዘረዘሩ ሰዎች አብዛኞቹ ትልልቁን ሥልጣን የያዙና የአካባቢው ዋነኛ የሚባሉትን አብዛኞዎቹን ሰዎች የሚያካትት በመሆኑ በንጉሱ ዘንድ አሳማኝና ለጥርጣሬ መንገድን የማይከፍት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።
4. እነዚህ በአካባቢያቸው እየኖሩ ያሉት ሳምራዊያንና አህዛቦች ለአይሁድ የእግዚአብሄር ማደሪያ እንደሆነች የሚያስቧትን ቅድስት ከተማ የተሰጧት ስሞች ዓመጸኛና ርኩስ ከተማ በሚል ስያሜ ነው የጠሯት። ሳምራዊያኑና ሌሎቹም ሰዎች ለእነዚህ ከባቢሎን ምርኮ ተመልሰው ስላሉት ሰዎች ሲናገሩ የምንሰማው እውነት ቢኖር ቅጥሮቿን እንደገና እየሰሩና መሰረቶቿንም በመጠገን ላይ መሆናቸውን መናገራቸው እነርሱም ሆኑ ማንም ሊክደው የማይችለው እውነት ነው።
5. እነዚህ ሰዎች ሃሳባቸው ተደማጭነት እንዲያገኝ የመረጡት ነገር የትልቁንም ሆነ የትንሹን ቀልብ የሚገዛውን የገንዘብን ነገር ነው አስታከው ያቀረቡለት፤ በተለይም ቁ13ትን ስናነብ በተለያየ መንገድ እያዟዟሩና ስሙን እየቀያየሩ የተናገሩትን ነገር ስንመለከት ዞሮ ዞሮ ከዚህ አካባቢ ይገኝ የነበረውን ገንዘብ አታገኝም የሚል ሃሳብ ነው። ለደብዳቤ መጻፋቸው ምክንያት አድርገው የጠቀሷቸው ሁለት ሃሳቦች፡ አንዱ ስለቤተ መንግሥቱ ስለሚገዳቸው፣ ሌላው ደግሞ የንጉስ ክብር ሲነካ ዝም ማለት ልክ ስላልሆነ ነው የሚሉት ናቸው።
6. ከውጭ ለሚመለከት ሰው የኢየሩሳሌምን መፈራረስና መውደቅ እነዚህ ሰዎች ምክንያት አድርገው ከሚሰጡት ነገር የተለየ ነገር ሊያቀርብ እንደማይችል ይመስለኛል፤ ሆኖም ይህች ከተማ የፈራረሰችበት እውነተኛው ምክንያት ግን ለሰራዊት ጌታ ለእግዚአብሄር ራሷን ለማስገዛትና በህጉ ለመኖር ፍቃደኛ ካለመሆን እንጂ በሌሎች ሃያላን ነገሥታት ላይ በማመጽ እንዳልሆነ እናውቃለን።
7. በንጉሱ የቤተ መዛግብት ምርመራ መሰረት የተገኘው እውነት፤ ኢየሩሳሌም የዓመጽና የወንጀል መናኸሪያ እንደነበረች፣ ከኤፍራጥስ ማዶ የነበረውን ሃገር ሁሉ የገዙ ነገሥታቶች እንደነበሯት፣ ከእነዚህ አገሮችም ሁሉ ቀረጥን፣ ግብርንና፣ እጅ መንሻንም ይቀበሉ እንደነበረ ተገኝቷል። ሬሁምና ሲምሳይ እንዲሁም ተባባሪዎቻቸው ሁሉ ከንጉሱ የደብዳቤ ምላሽ አግኝተው መቼ ስራውን ባስቆምናቸው በሚል ቸኩለው እንደነበረ የሚጠቁመን ሃሳብ በቁ23 ላይ እንደምናየው ሳይውሉና ሳያድሩ ወዲያው ደብዳቤውን እንዳገኙ ሄደው ማስቆማቸው የነበራቸውን የማስተጓጎል ፍላጎት ይጠቁመናል።
8. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የአይሁድ ጠላቶች የቤተ መቅደሱን ሥራ ለማስቆም የተጠቀሙባቸው አራት ታክቲኮች የሚከተሉት ናቸው፡ የመጀመሪያው እነርሱ የቆሙለትንና ሊሰሩ ያሰቡትን ሥራ በተባባሪነት ራሳቸውን ለማስገባት በመሞከር፣ ሁለተኛው ሕዝቡን ተስፋ ለማስቆረጥ ሥራውን እንዳይቀጥሉ የማስፈራራት ዘመቻ በማካሄድ፣ ሶስተኛው ደግሞ ቤተ መቅደሱን የመስራት ዕቅዳቸውን የሚያሰናክሉ መካሪዎችን በገንዘባቸው መቅጠርና፣ አራተኛና የመጨረሻው ደግሞ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ላይ የጽሑፍ ክስን መመስረት ነበሩ።

<u>ጥናት አራት ዕዝራ 5፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በትንቢተ ሐጌ የመጀመሪያው ምዕራፍ ቁ2 ላይ በምናነብበት ጊዜ ሕዝቡ ስለነበረበት መንፈሳዊ ሁኔታና ቤተ መቅደሱን መስራት በሚለው ሃሳብ ዙሪያ ምንም ለመንቀሳቀስ የማይፈልግበት፣ ሁሉም ኑሮዬን ብቻ ልኑር በሚል አመለካከት የተዋጠበት ጊዜ እንደነበረ ነው መረዳት የምንችለው። በዚህ ክፍል ነብያቱ ሐጌና ዘካርያስ የትንቢታቸው ምንጭ ማን እንደሆነና ከየት እንደተቀበሉት ሲናገሩ፤ "ከእነርሱ በላይ በሆነው በእስራኤል አምላክ ስም ትንቢት ተናገሩላቸው።" በማለት የትንቢቱን ምንጭ ያረጋግጣሉ።
2. ተንትናይና ሰተርቡዝናይ እንዲሁም ተባባሪዎቻቸው አይሁድንና መሪዎቻቸውን የጠየቋቸው ሁለት ጥያቄዎች፡ የመጀመሪያው ጥያቄ "ይህንን ቤተመቅደስ እንደገና ለመሥራትና ውቅሩንም ለመጠገን የፈቀደላችሁ ማን ነው?" ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "ይህንን ህንጻ የሚገነቡት ሰዎች ስም ማን ይባላል?" የሚል ነው። ቤተ መቅደሱ ቀድሞ ተጀምሮ የቆመ ሥራ እንደሆነ እንደሚያውቁ የሚጠቁመን ሃሳብ በቁ3 ላይ "እንደገና ለመሥራት" የሚለው አነጋገራቸው ያስረዳናል።
3. እነዚህ በይሁዳና በኢየሩሳሌም አካባቢ የሚገኙት ባለሥልጣኖችና ገዢዎች የተጀመረውን የእግዚአብሄር ሥራ ለማስቆም ያልቻሉበትን ምክንያት ለማወቅ የቁ5ትን ሃሳብ እንደገና ማንበብ ይረዳል፤ "የአምላካቸው ዓይን ግን በአይሁድ መሪዎች ላይ ነበረ" የሚለው ሃሳብ ጠላቶቻቸው ሊከለክሏቸው አለመቻል ምክንያት ሆኖ ነው የተነገረው።
4. ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው በጊዜው የባቢሎን ንጉስ ለነበረው ለንጉሥ ዳርዮስ በጻፉት የክስ ደብዳቤ ላይ የእስራኤልን አምላክ የጠሩበት ሥም ቁ8 እንደሚነግረን "ታላቁ አምላክ" የሚል ስያሜ ነው የሰጡት። ቁ8 ላይ ማየት እንደምንችለው ከጠላቶቻቸው አመለካከት የቤተ መቅደሱ ሥራ እየተሰራ ያለው በህዝቡ ሁሉ እንጂ በጥቂቶች ሰዎች እንዳልነበረም እንረዳለን።
5. እኔ እንደሚመስለኝ እነዚህ የአይሁድ ጠላቶች ለንጉሥ ዳርዮስ ሊያስተላልፉ የፈለጉት መልዕክት የነህምያ ጠላቶች የሰሩትን ቅጥር "ቀበሮ እንኳን ብትወጣበት ሊፈርስ ይችላል" እንዳሉት ሳይሆን ሥራቸው የዋዛ እንዳልሆነና ንጉሥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር እንደሆነ ለማስገንዘብ ይመስለኛል።
6. የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች ቤተ መቅደሱን መስራት በመጀመራቸው እንደተከሰሱ በምናይባቸው በሁለቱም ጊዜያት፤ በባቢሎን ላይ የነገሱት ነገሥታት እንዲያደርጉ የተጠየቁት አንድ ነገር ቢኖር በባቢሎን ግምጃ ቤት ተቀምጠው የነበሩትን መዛግብት እንዲመረምሩና ክሱ ትክክል መሆን አለመኖሩን እንዲያረጋግጡ ነበረ።
7. የይሁዳና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ወይም አይሁዳውያኑ ከጠላቶቻቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ በቁ11 ላይ ለእግዚአብሄር ሲሰጡት የምናየው ሥም "የሰማይና የምድር አምላክ" የሚል ነበረ።
8. እነ ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው አይሁዶቹ ቤተ መቅደሱን በጥሩ ሁኔታና ጥራት ባለው መልክ እየሰሩት እንዳሉ ብቻ ሳይሆን፤ ነገር ግን ሕዝቡ ሥራውን ትጋት በተሞላው መልኩ፣ ፍጥነት በተሞላው መንገድ እየተሰራ እንደሆነ ስለሥራውም ሆነ ስለ ሰራተኞቹ ጥሩ የሆነ ግምገማ እንዳደረጉ ማየት ይቻላል።

# ጥናት አምስት ዕዝራ 6፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ በአሕምታ ከተማ ውስጥ እንደተገኘ የተነገረው አንድ ጥቅልል ብራና በዚያን ጊዜ በነበሩት አይሁድ ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥለውም ትውልድ ሁሉ የሚተርፍ ውጤት ነበረው ብዬ አምናለሁ፤ ምክንያቱም ንጉሥ ዳርዮስ ያንን ብራና ባያገኝ የቤተ መቅደሱን ሥራ እንዲቀጥል አያውጅም ነበረና ነው። እግዚአብሄር ነገሮችን ሲያቀነባብር የዛሬን ብቻ ተመልክቶ ሳይሆን ወደፊት ሊመጣ ያለውን ሁሉ ተመልክቶ ነገሮችን ማቀነባበር የሚችል አምላክ እንደሆነ መማር እንችላለን።
2. በዚህ ላይ በምናነበው የንጉስ አዋጅ ውስጥ ተጠቃለው የማያቸው ሁለቱ ዋና ዋና ሃሳቦች፤ የመጀመሪያው ዋና ሃሳብ ብዬ የምለው ቤተ መቅደሱ ከቤተ መንግሥት ግምጃ ቤት ውስጥ ወጪ ሆኖ እንደገና እንዲሰራ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የቀደመው ንጉሥ ናቡከደነጾር ከእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ አውጥቶ ወደ ባቢሎን የወሰዳቸው የወርቅና የብር እቃዎች በሙሉ በኢየሩሳሌም ሊሰራ ወደታቀደው ቤተመቅደስ እንዲመለሱና በዚያ እንዲቀመጡ የሚሉት ናቸው።
3. እነዘሩባቤል በዕዝራ 4፡2-3 ላይ አብረን እንስራ፣ ሥራው እኛንም ይመለከተናል ለሚለው የአካባቢው ሰዎች ጥያቄ፣ ሥራው የእኛ እንጂ እናንተን አይመለከትም ብለው እንደመለሱ፤ በዚህ ሥፍራም ንጉሱ የተናገራቸው ነገር ሥራውን መሥራት ያለባቸው እነርሱ ናቸው፣ እናንተ ከዚህ ውስጥ እጃችሁን አውጡ በማለት በትክክል እነርሱ አስቀድመው የተናገሯቸውን ሃሳብ ነበር ንጉሱ በማስጠንቀቂያ መልክ የተናገራቸው።
4. እነዚህ የአይሁድ ጠላቶች ሳይወዱ በግዳቸው ከቤተ መንግሥት ግምጃ ቤት የሚጠየቀውን ያህል ገንዘብ እያወጡ ለእስራኤላውያን በመስጠት እንዲተባበሯቸው የታዘዙት ሁለት ዋና ዋና ነገሮች፤ አንደኛው የቤተ መቅደሱ ሥራ በምንም ምክንያት ሳይቋረጥ እንዲሰራ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማሟላት እንደሚኖርባቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ መቅደሱ ተሰርቶ ካበቃ እንኳን በኋላ ለመስዋዕትነት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ ምንም ሳይጓደል ማቅረብ እንደሚኖርባቸው ነው የታዘዙት።
5. ንጉሱ ቤተ መቅደስ የሚሰራበትንም ሆነ ቀጥሎም የሚሰዋውንም መስዋዕት ጨምሮ ከመንግሥት ካዝና እንዲወጣና አስፈላጊው ሁሉ አምልኮ ሁሉ እንዲካሄድ ትዕዛዝ የሰጠበትን ምክንያት በቁ10 ላይ ሰፍሮ እናገኛለን፤ እንዚህም ምክንያቶች የሰማይን አምላክ ደስ የሚያሰኝ መስዋዕት እንዲቀርብና፤ ሌላኛው ደግሞ ለንጉሱና ለቤተሰቡ እንዲጸለይ በማለት ነው። ንጉስ ዳርዮስ አዋጁን ባቃለለና በቤተ መቅደሱ ላይ እጁን አነሳለሁ ባለ ማናቸውም ሰው ላይ ራሱ ከሚወስደር እርምጃ ባሻገር በመቅደሱ ውስጥ የሚኖረው ሃያሉ አምላክ ተጨማሪ ቅጣት እንዲያመጣበትም ይመኛል።
6. በቁ13 እና በቁ14 ውስጥ ብቻ ለቤተ መቅደሱ መሰራት መጠናቀቅ አስተዋጽዖ እንዳደረጉ የማያቸው ሰዎች፡ የአይሁድ መሪዎች፣ ነብያቱ ሃጌና ዘካርያስ፣ ሶስቱ የፋርስ ነገስታት ቂሮስ፣ ዳርዮስና፣ አርጤክስስ፤ በውዴታም ባይሆን በግዴታ አስተዋጽዖ ያደረጉ ደግሞ ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው ይገኙበታል።
7. በዚህ ቁጥር ላይ እግዚአብሄር በንጉሱ ልብ ላይ ስላከናወነው ተግባት ስናነብ መረዳት የምንችለው ነገር ቢኖር፤ በእግዚአብሄርና በሰው መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት፤ ያም ከእግዚአብሄር በስተቀር የሰውን ልብ ለውጦ የፈለገውንና ያሰበውን ነገር ማድረግ የሚችል ሌላ ማንም እንደሌለ የሚያስገነዝበን ክፍል ነው።
8. የእስራኤል ሕዝብ በዚህን ወቅት ደስ ሊሰኙ የሚችሉበት የቤተ መቅደሱ መጠናቀቅ፣ ከማያስቧቸው ከጠላቶቻቸው እንኳን ይህ ነው የማይባል እርዳታ እንዲያገኙ መደረጉ፣ የእግዚአብሄር ነብያት የሆኑት ሐጌና ዘካርያስ በሚያጽናኑ ቃላት እየደገፉ ማገዛቸውና ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች እንደነበሯቸው ቢታወቅም እንኳን፤ ጸሐፊው በቁ22 ላይ ሲነግረን ግን የእነዚህ ሰዎች ልብ በደስታ የመሞላቱን ምክንያት "እግዚአብሄር ደስ ስላሰኛቸው" በማለት የደስታቸው ምንጭ እግዚአብሄር እንደሆነ ይነግረናል።

## ጥናት ስድስት ዕዝራ 7፡1-28 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ፤ ይህንን ያህል ወደኋላ ሄዶ የዚህን ሰው የዘር ግንድ እስከ አስራ ስድስት ትውልድ ድረስ መቁጠር ያስፈለገበት ምክንያት እንዲሁ ከካህናት ዘር የሆነ ከማለት ይልቅ ዕዝራ የታላቁ የእስራኤል ካህን ከአሮን ዘር መሆኑን ለመናገር የፈለገ ይመስለኛል። ምንም እንኳን መጽሐፉ በእርሱ ስም ቢጠራም ቤተ መቅደሱን ከመስራት አኳያ የዕዝራ እጅ አልነበረበትም፤ ቤተ መቅደሱን በዋነኛነት ከህዝቡ ጋራ የሰሩት ኢያሱና ዘካርያስ ነበሩ።
2. ዕዝራ ይኖር የነበረው በባቢሎን ነበረ፣ በፋርስ ንጉስ በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት ወደ ኢየሩሳሌም መጣ፣ እግዚአብሄር ለሙሴ የሰጠውን ሕግ በሚገባ የሚያውቅ የህግ መምህር ነበረ፣ የእግዚአብሄር እጅ በእርሱ ላይ ነበረች፣ ለንጉስ ጥያቄ አቅርቦ የተፈቀደለት ሰው ነበረ። ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሰበት ወቅት ወደ አገራቸው የተመለሱት ሰዎች ቁ7 እንደሚነግረን፤ ከካህናት፣ ከሌዋውያን፣ ከመዘምራን፣ ከበር ጠባቂዎችና፣ ከቤተ መቅደስ አገልጋዮች ጋራ በመሆን የተመለሱ እስራኤላውያን እንደነበሩ እናነባለን።
3. ቁ9 ላይ ዕዝራ ጉዞውን የጀመረበትን ቀን ስንመለከት በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ወር ላይ ሲሆን፣ ኢየሩሳሌም የደረሰበትን ቀን ደግሞ ስናይ በአምስተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ስለሆነ በአጠቃላይ ጉዞው የወሰደበት ቀን አራት ሙሉ ወራት እንደሆነ መረዳት እንችላለን። መልካሚቱ የእግዚአብሄር እጅ በእርሱ ላይ መሆን ለዕዝራ የጠቀመ ብዬ የማምነው፤ በመጀመሪያ ደረጃ ሊያገኘው ከሚችለው አደጋ ሁሉ መጠበቁን አስመልክቶ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ያንን ሁሉ ጉዞ ሕመምና በሽታ ሳይደርስበት በሰላም መድረሱ ከመልካሚቱ የእግዚአብሄር እጅ የተነሳ እንደሆነ ለመናገር ይመስለኛል።
4. ዕዝራ ቁ10 እንደሚናገረው የእግዚአብሄርን ቃል አስመልክቶ ራሱን ፈጽሞ የሰጠላቸው ወይም የተሰጠላቸው ሶስቱ ነገሮች፡ አንደኛው የእግዚአብሄርን ቃል ለራሱ ማጥናት ነበረ፤ ሁለተኛው ከቃሉ የተማረውን ነገር በህይወቱ ተግባራዊ የማድረግ ነገር ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ ቃሉን ካጠናና በህይወቱ ካዋሃደ በኋላ ለሌሎች ማስተማር ነበረ። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጸሐፊው ለዕዝራ መጠሪያ አድርጎ የተጠቀመባቸው ሁለቱ መጠሪያዎች ካህንና መምህር የሚሉት ናቸው።
5. ዕዝራ ከንጉሱ በተሰጠው መመሪያና ትዕዛዝ መሰረት በጉዞው ወደ ኢየሩሳሌም ወስዶ ለእግዚአብሄር ቤት አገልግሎት እንዲያውለው በቁ13-16 ውስጥ የተነገረው፤ ከንጉሱና ከአማካሪዎቻቸው በፈቃዳቸው የሚሰጠውን ስጦታና፣ ከመላው ባቢሎን ሕዝብ የሚገኝ ስጦታና፣ የእስራኤል ህዝብና ካህናቱ ለአምላካቸው የሚሰጡትን ስጦታ ነበረ እንዲወስድ የተነገረው። ምንም እንኳን ብዙዎች ዕድሉን ሲጠቀሙበት ባይታይም፤ በዚያን ወቅት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ ፈቃድ የተሰጣቸው ለማናቸውም መሄድ ለፈለገ ሁሉ ነበረ።
6. ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱሳችን ከዚህ አስቀድሞ በዕዝራና በንጉሱ መካከል ስለነበረው ግንኙነት ግልጽ አድርጎ ባያሰፍርልንም፤ ንጉሱ በቁ11 እና 12 ላይ ስለዕዝራ ከሚናገራቸው አነጋገሮች እምነት ሊጣልበት የሚችል ሰው እንደነበረ ስለተረዳ ይመስለኛል።
7. ዕዝራ አምላኩን እግዚአብሄርን የሚያመሰግንባቸው የእግዚአብሄር ቤት በዚህ ሁኔታ ክብር እንዲያገኝ በንጉሥ ልብ ውስጥ ስላስቀመጠና ሌላው ደግሞ በንጉሱ፣ በአማካሪዎቹና በሃያላን ሹማምንቱ ፊት ሞገስ ስለሰጠው እግዚአብሄርን ያመሰግናል። ካህኑ ዕዝራ ከእርሱ ጋራ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ የሚፈልጋቸውን የታወቁ ሰዎች ለማሰባሰብ ስለቻለበት ሁኔታ ሲነግረን "የእግዚአብሄር እጅ በእኔ ላይ ስለነበረች" ነው በማለት ነው የሚያስረዳን።
8. እንደ እኔ አመለካከት ከሆነ፤ ምንም እንኳን ቃሉን ማጥናትና ያጠናነውንም ደግሞ ለሌሎች እንዲጠቅም ማስተማር የሚሉት ሃሳቦችም እንደምንቸገርባቸው ቢገባኝም፤ በራሴም ሕይወት ሆነ በአካባቢዬ የማያቸው ብዙዎች ወንድሞችና እህቶች ሲደናቀፉበት የማየው ነገር ቃሉ ከማጥናትና ከማስተማር ይበልጥ ከቃሉ የተማርነውን ነገር በሕይወታችን በተግባር ለመተርጎም የምናሳየው ቁራጥነት ዝቅተኛ እንደሆነ ይመስለኛል።

# <u>ጥናት ሰባት ዕዝራ 8፡1-36 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ወደ እናት ሃገሩ ወይም ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ የተደረገውን ጥሪ በመቀበል እያንዳንዱ እስራኤላዊ በየግሉ ጉዞውን ቢጀምርና በአህዋ የተደረገው መሰባሰብ እንዲሁም የሶስት ቀናት ቆርታ ባይካሄድ ኖሮ ከሌዊ ወገን የሆነና ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት ከሚያስፈልጉት ዋነኛ አንድም ሰው ሳይሄድ ለአገልግሎቱ መተጓጎል ትልቅ ምክንያት ይሆን እንደነበረ ይመስለኛል። በተለያዩ ሥፍራዎች መልካሚቱ የአምላካቸው እጅ ያከናወነችው ነገር ሲኖር፤ በዚህ ቦታ ደግሞ ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት አስፈላጊ የነበሩትን ሌዋውያኑን በበቂ ቁጥር እንዲገኙ በማድረግ አግዛለች።
2. ቁ21 ላይ እንደምናነበው ገና ከባቢሎን ተነስተው የመጡት ሌዋውያኑ ከእነርሱ ጋራ እንደተቀላቀሉና ከሰፈሩበት ከአህዋ ሳይወጡ አስቀድመው ሶስት ቀናት የሚቆይ ጾምን በማወጅ የአምላካቸውን ፊት ለመፈለግ እንደተነሱ እናነባለን። ዕዝራና ከእርሱ ጋራ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች ሁሉ መጾምና መጸለይ ስላስፈለጋቸው ምክንያት ቁ21 ግልጽ አድርጎ ይናገራል፤ ይህም ምክንያት ጉዟቸውን በሚያደርጉበት ወቅት የአምላካቸው ጥበቃ በራሳቸው፣ በቤተሰባቸው፣ በልጆቻቸውና በንብረታቸው ላይ ሁሉ እንዲሆን ነበረ።
3. ዕዝራ ለራሱና ከእርሱ ጋራ ለነበሩት በሙሉ እንዲሁም በእጃቸው ለነበረው ንብረት ደህንነትና ጥበቃን አስመልክቶ ያደረገው ነገር ቢኖር እግዚአብሄር እንዲጠብቃቸው በጾምና በጸሎት መለመን ሲሆን፣ ነህምያ ደግሞ በበኩሉ ከንጉሱ ጠባቂዎች እንዲመደቡለትና የሚሄድበት ድረስ እንዲሸኙት መጠየቅ ነበረ። ሁለቱም የጌታ ባሪያዎች ያደረጉት ነገር በአምላካቸው ላይ በመታመን እንደነበረ ነህምያ በንጉሱ ፊት ሞገስ ያገኘውና የተፈቀደለት መልካሚቱ የአምላኩ እጅ በእርሱ ላይ ስለነበረች እንደነበረ በቁ8 ላይ መናገሩን ስናይ፤ የእርሱም ድርጊት በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት እንደነበረው ይጠቁመናል።
4. ነህምያ በቁ21 ላይ ሲናገር እንደምንመለከተው ጥበቃውን አስፈላጊ ሆኖ ያገኘባቸውን ሶስት ምክንያቶች ይነግረናል፤ አንደኛው "ለእኛ" ያለው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የወሰኑትን ሰዎች ሲሆን፤ ሁለተኛው "ልጆቻችን" የሚላቸው ምናልባትም ከቤተሰብ ውሳኔ የተነሳ የሚመለሱትን ሕጻናት፤ ሶስተኛው ደግሞ "ንብረታችን" የሚለው ብዙ ቁጥር የነበረውን ብር፣ ወርቅና የመሳሰሉትን ይጨምራል። በዕዝ 4፡3 ላይ እንቢ የተባሉትን ሰዎች ስናይ ክፍሉ እንደሚገልጸው ሥራውን ለማከሸፍና ለማበላሸት የተጠነሰሰ እንጂ ከቅን ልብ እንዳልነበረ ሲታወቅ፣ ንጉሱ ግን በብዙ በተለያዩ መንገዶች ማለትም ጉዞውን ከመፍቀድ አንስቶ እግዚአብሄር ያነሳሳው መሆኑን በግልጽ ማየት ይቻላል።
5. ለእግዚአብሄር ቤት ሥራ የሚያስፈልገውን ማናቸውንም ዓይነት ነገር በመለገሥ የተባበሩት ሰዎች፡ ንጉሥ አርጤክሥ፣ የንጉሥ አማካሪዎች፣ የንጉሱ ሹማምንትና እንዲሁም በባቢሎን ይኖሩ የነበሩትን እስራኤላውያን ይጨምራል። "እናንተና እነዚህ እቃዎች ለእግዚአብሄር ተቀድሳችኋል" ማለቱ ካህናቱ ለእግዚአብሄር ሥራ የተለዩ ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን፣ ለእግዚአብሄር ቤት ሥራ የተሰበሰበውም ወርቅ፣ ብርና ሌሎቹም ነገሮች ሁሉ የሰው ንብረቶች ሳይሆኑ ለእግዚአብሄር አገልግሎት የተለዩ ናቸው ማለት ነው።
6. ዕዝራ ከንጉሥ አርጤክሥ ገንዘብንና ንብረትን አስመልክቶ የተሰጠው ገደብ ያልተጣለበት ሥልጣን ህይወቱን እንዳይቦረቡርበት የተጠቀመበት ዘዴ፤ ለብቻው እርሱ የሚያዝበት ነገር አድርጎ ሳይዝ በሌሎች እጅ እንዲጠበቅና እንዲያዝ በማድረግ ነበረ።
7. ይህ የህዝብ መሪ የሆነ ሰው ዕዝራ በእነዚህ አሥራ አንድ ቁጥሮች ውስጥ ሰዎች ለእግዚአብሄር አገልግሎት ብለው በፈቃደኛነት የሚሰጡት ማንኛቸው ዓይነት ንብረትም ሆነ ገንዘብ በብዙ ጥንቃቄ መያዝ እንደሚኖርበት፣ ለመቁጠር፣ ለመመዘንና፣ ለመረካከብናም ሁሉ በአንድ ሰው እጅ ብቻ መደረግ እንደማይኖርበት ግልጽ በሆነ መንገድ ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎችን ሊያሳትፍ የሚገባው ነገር እንደሆነ ሲጠቁመን፤ በእኛም ዘመን ያለች ቤተ ክርስትያን ከእግዚአብሄር ሰው ከዕዝራ ጥበብ የተሞላ አሰራር ተምራ ገንዘብ ሊያስከትል ከሚችለው አደገኛ ወጥመድ ራሷን ልትጠብቅ እንደሚገባት መማር እንችላለን።

# ጥናት ስምንት ዕዝራ 9:1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጸሐፊው በመከፈቻው አረፍተ ነገር ላይ ተፈጸሙ የሚላቸው ነገሮች በዕዝራ ምዕራፍ 8 ላይ ዕዝራ እንዲከናወኑ በሙሉ ሃይሉ የጣረላቸው ከንጉሱ፣ ከሹማምንቱ፣ ከመኳንንቱና በባቢሎን ይኖሩ ከነበሩት እስራኤላውያን የሰበሰበውን ወርቅ፣ ብርና ሌሎችንም ነገሮች ሁሉ ቆጥሮ ለሚመለከታቸው ሰዎች ካስረከበ በኋላ ማለቱ ነው። እነዚህን ሁለት መሪዎች የሚለያቸው አንድ ነገር ቢኖር፤ በቁ1 ላይ የሚታዩት መሪዎች ሕዝቡ እግዚአብሄርን ከመበደል እንዲመለስ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ሲሆኑ፣ በቁ2 ላይ የምንመለከታቸው መሪዎች ደግሞ ሕዝቡን እግዚአብሄርን መበደል ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች ናቸው።
2. እግዚአብሄር የእስራኤል ልጆች ገና በምድረበዳ ሳሉ የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ይህ ቁ1-2 ያለው ክፍል የሚያረጋግጥልን መንገድ ቢኖር፤ እነዚህ ቅሬታዎች ሆነው ከባቢሎን የተመለሱት እስራኤላውያን ከአህዛብ ጋራ በመጋባታቸው ምክንያት እግዚአብሄር እንዳስጠነቀቃቸው የአህዛብን ርኩሰት ወደመለማመድ እንደወሰዳቸው ቁ1 ያረጋግጥልናል። በዚህ ክፉ ሥራ ላይ እንደተሳተፉ የምናያቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፡ በቁ1 ላይ ካህናቱና ሌዋውያኑ እንዳሉበት ይነግረናል፣ ቁ2 መሪዎቹና ሹማምንቱ እንደነበሩበት ሲነግረን፣ ተራው ህዝብም በዚህ ተግባር እንደተሳተፈ ቁ1 ላይ ማየት ይቻላል።
3. መሪያቸውን ነህምያን የሚገኝበትን የሐዘን ልብ ለመጋራት ወደ እርሱ የመጡት ሰዎችን ማንነት ቁ4 ሲናገር “በእስራኤል አምላክ ቃል የተንቀጠቀጡ ሁሉ በዙሪያዬ ተሰበሰቡ።” በማለት የሚናገራቸው ናቸው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምንመለከታቸው ሰዎች እውነትም በተከሰተው ሃጥያት ውስጥ ተሳትፎ አልነበራቸውም፤ ሆኖም እግዚአብሄርን የሚፈሩና ለእግዚአብሄር ሥም የሚቀኑ ዓይነት ሰዎች በመሆናቸው ሃጥያት ከመሃላቸው መገኘቱ የሚከነክናቸውና መወገድ እንደሚኖርበት የተገነዘቡ ስለሆኑ ነው።
4. እግዚአብሄር በኢሳይያስ 66:2 ላይ በቃሉ ስለሚንቀጠቀጡ ሰዎች ሲገባ የምናየው ቃል ኪዳን ወደ እነርሱ እንደሚመለከት፣ ማለትም ፊቱን ወደ እነርሱ እንደሚመልስ ነው። እነዚህን ሁለት ታላላቅ መሪዎች ስንመለከት ሁለቱም የእግዚአብሄር ሕዝብ ውድቀትና እግዚአብሄርን መበደል ውስጣቸው የሚገባና የሚያስለቅሳቸው ሰዎች መሆናቸው ከሚያመሳስሏቸው ነገሮች አንደኛው ነው።
5. ምንም እንኳን ዕዝራ በሰማው ክፉ ዜና ተደናግጦ ሃዘኑን ለመግለጫ የተጠቀመባቸው የተለያዩ ነገሮችን በማድረግ እንደገለጸ ብንመለከትም፤ እነዚያን ነገሮች ብቻ አድርጎ ማቆሙ በቂ ሆኖ ስላላገኘው ወደሚቀጥለውና ደረጃ እንዳለፈ እናያለን፤ ያም እርምጃ ቁ5 እንደሚነግረን በጸሎት ወደ እግዚአብሄር ፊት መቅረብ ነው። ዕዝራን ወደ እግዚአብሄር በድፍረት ለመምጣት አሳፋሪ ሆኖ ያገኘው ነገር ቢኖር በቁ7 ላይ የተናገረው “ከአባቶቻችን ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በደላችን ታላቅ ነው።” የሚለው ሃሳብ ነው።
6. እንደ ዕዝራ አመለካከት የእስራኤል ሕዝቦች ዛሬ ስለሚገኙበት ሁኔታም ሆነ እያለፉ ላሉበት አስከፊ ሁኔታ በሃላፊነት ሊጠየቁ የሚገባቸው ራሳቸው እስራኤላውያኑ እንጂ እግዚአብሄርን በምንም ዓይነት በሃላፊነት መጠየቅ እንደማይቻል ነው ጸሎቱ የሚያረጋግጥልን። ከእነዚህ ቁጥሮች የእግዚአብሄርን ቸርነት የሚያሳዩት፤ “…ለጥቂት ጊዜ ቸርነቱን አሳይቶናል፣ በባርነት ሳለን ለጥቂት ጊዜ እረፍት ሰጠን፣ ባሮች ሆነን እንድንቀር አልተወንም፣ በፋርስ ነገስታት ፊት ቸርነቱን አሳየን፣ የአምላካችንን ቤት እንደገና እንድንሰራና ፍርስራሾቿን እንድንጠግን አዲስ ህይወት ሰጠን፣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም የመከላከያ ቅጥር ሰጠን” የሚሉት ይገኙበታል።
7. በቁ10-12 ላይ ዕዝራ ያተኮረበትና በጊዜው አጥፍተናል ብሎ የሚናዘዝበት ሃጥያት እግዚአብሄር አስቀድሞ ከአህዛብ ሴቶችን ለራሳቸው እንዳይወስዱና እነርሱም ልጆቻቸውን ለእነርሱ እንዳይሰጡ ያዘዘውን ትዕዛዝ መተላለፋቸውን ነበረ።
8. በዚህ ክፍል ውስጥ ለእግዚአብሄር ቃል መንቀጥቀጥ የሚለውን አነጋገር የምረዳው፤ እግዚአብሄር የሚናገረውን ነገር በድፍረትና ንቀት በተሞላው መንገድ ሳይሆን ሰዎቹ የእግዚአብሄርን ቃል በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ማስተናገድ ብቻ ሳይሆን እርምጃ ለመውሰድም የወሰኑ ሰዎች መሆናቸውን ነው የማስተውለው።

# ጥናት ዘጠኝ ዕዝራ 10፡1-44 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ምንም እንኳን ዕዝራ በሃጥያቱ ውስጥ እጁን ባያስገባም፤ ልክ እርሱም እዚያ ውስጥ እንደነበረ አድርጎ በእግዚአብሄር ፊት ሲያለቅስ፣ ሲናዘዝና፣ ንስሃ ሲገባ ነው የምንመለከተው። ሕዝቡ ዕዝራ በዚህ ዓይነት መንገድ ራሱን በእግዚአብሄር ፊት ሲያዋርድና ሲጸልይ አይተው እጅግ ብዙ ሕዝብ መጥተው ከእርሱ ጋራ እንደተባበሩ እናነባለን። ከዚህ ሁኔታ መማር የሚቻለው ትልቅ እውነት ቢኖር፤ መሪ ከቃላት አልፎ ትክክለኛውን መንገድ በሕይወቱ ካሳየ፤ ሕዝብ ለመከተል ወደኋላ እንደማይል ነው።
2. በዚህ ሰው ንግግር ውስጥ በሃዘን ለተመታው ለእግዚአብሄር ሰው መነቃቂያ ሊሆኑ የሚችሉት ሁለቱ ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡ የመጀመሪያው በቁ2 ላይ የምናየው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ብንገኝ አሁንም ተስፋ አለ የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቁ4 ላይ የሚገኘውና ዕዝራ ብቻውን እንዳልሆነና ህዝቡ አብረውት እንደሚቆሙ የተናገረው ሃሳብ ነው። ይህንን ማወቅ የሚቻለው በቁ2 ላይ "በዙሪያችን ካሉት አሕዛብ፣ ባዕዳን ሴቶችን በማግባታችን ለአምላካችን ታማኞች ሆነን አልተገኘንም" በማለት መናገሩ ይህንን እውነት ያረጋግጥልናል።
3. በዚህ ክፍል ውስጥ የዕዝራ ሐዘን እንዲያው ዝም ብሎ ለማስመሰልና ለታይታ እንዳልነበረ የሚጠቁመን ሃሳብ በቁ6 ላይ የምናነበው ሃሳብ ነው፤ ቁ7ትን ስንመለከት ለቅሶውን ማቋረጥ እንኳን እንዳልቻለና፤ ምግብና መጠጥም እንዳልቀመሰ በግልጽ ይናገራል። ይህ መፍትሄን ለመፈለግ ሊደረግ ያለው ስብሰባ ክብደት እንደተሰጠው የሚጠቁመህ በቁ8 ላይ የተነገረው ሲሆን፤ ንብረትን ሁሉ ከማጣት አልፎ ከምርኮኞች ጉባኤ መባረርን ሁሉ የሚያካትት መሆኑ የቀልድ እንዳልሆነ ያሳየናል።
4. ሕዝቡ እንደተጨነቁባቸው አድርጎ በተለይም ቁ9 እንደሚነግረን "ስለ ወቅቱ ጉዳይና ስለ ከባዱ ዝናብ በመጨነቅ በእግዚአብሔር ቤት ፊት ባለው አደባባይ ተቀምጠው ነበር።" በማለት የተሰበሰቡበት የሃጥያት ጉዳይና፤ ከባድ በሆነ ዝናብ ላይ የመሆናቸው ጉዳይ አስጨንቋቸው ነበረ። በምዕራፍ 9፡6 ላይ ለእግዚአብሄር ሲናገር ራሱንም ከበደለኞች መሃል ጨምሮ ሲሆን፤ በዚህ ክፍል በቁ10 ላይ ለህዝቡ ሲናገር ግን በቀጥታ ጥፋቱን ባጠፉት ሰዎች ላይ ነበረ ያተኮረው።
5. ሕዝቡ የስብሰባ ጊዜው እንዲቀየር ባቀረቡት ሃሳብ ላይ በምክንያትነት የተጠቀሙባቸው ሁለቱ ነገሮች፤ የመጀመሪያው ወቅቱ ክረምት በመሆኑ ዝናቡና ቅዝቃዜው ሕዝቡን ስለሚያስቸግር፤ ሁለተኛው ደግሞ የሃጥያቱ ብዛትና አስከፊነት ሰፋ ያለ ጊዜ ስለሚጠይቅ ነው። አስቀድመን ቁ12 እንደሚያሳየን በሚያስማማን ሃሳብ መጀመር፤ ሌላው ደግሞ ችግርን ብቻ ከመሰንዘር መፍትሄውንም አብረን ለማቅረብ መሞከር መልካም ትምህርት ይሆነናል ብዬ አምናለሁ።
6. አራቱ ሰዎች ተብለው የተጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው። "ይህንንም ነገር የተቃወሙት ከሜሱላምና ከሌዋዊው ከሳባታይ ድጋፍ ያገኙት የአሣሄል ልጅ ዮናታንና የቴቁዋ ልጅ የሕዝያ ብቻ ናቸው።" የሌዋዊው ስም እዚህ ውስጥ መገኘቱ እኔን አስገርሞኛል።
7. በዚህ ክፍል የምናያቸው አምስቱ ምድቦች፡ 1ኛ) ካህናት ቁ18 2ኛ) ሌዋውያን ቁ23 3ኛ) መዘምራን ቁ24 4ኛ) በር ጠባቂዎች ቁ24 እና 5ኛ) ሌሎች እስራኤላውያን በማለት በቁ25 ላይ የሚናገራቸው ይገኙበታል። እነዚህን አምስት ዝርዝሮች ስንመለከት በተለይ የመጀመሪያዎቹ አራቱ በተለያየ አገልግሎት ላይ ያሉ ሲሆን፤ አምስተኛውን ስናይ ግን ይህ ሃጥያት ያልዳሰሰው ዓይነት ሰው እንደሌለ ያረጋግጥልናል። ይህ የሚያስተምረን ሃጥያት አገልጋይንም ሆነ ማንኛውንም ዓይነት ሰው እንደማይፈራና ሰው ሁሉ ተጠንቅቆ መኖር እንደሚኖርበት ነው።
8. የእግዚአብሄር ሰው ስለሆነ ስለ ዕዝራ በምዕራፍ 7 ውስጥ የምናየው አንደኛ ገጽታውን ማለትም የእግዚአብሄርን ቃል አስመልክቶ ያለውን አክብሮትና አመለካከት ሲሆን፤ በዚህ በምዕራፍ 10 የመጀመሪያውን ቁጥር ስንመለከት ደግሞ ለዚህ ሰው ከእግዚአብሄር ጋራ ላለው ሕይወት ተጨማሪ ውበት ያጎናጸፈውን ሌላኛውን ገጽታ የምናይ ሲሆን፤ ይህም የጸሎት ሰው መሆኑ ነው።